Fact Sheet

**ሴንትራል ኮሪዶር (ወይም መሃከለኛው መተላለፊያ) ምንድን ነው?**

• ሴንትራል ኮሪዶር 11 ማይል ርዝመት ያለው ሚኒያፖሊስን ከዳውንታውን ሴንት ፖልና ከዩኒቨርሲቲ ኦፍ ሚኔሶታ እንዲሁም በመሃከል የሚገኙትን በርካታ የመኖሪያና የንግድ ሠፈሮች የሚያገናኝ መጓጓዣ መንገድ ነው።

**በሴንትራል ኮሪዶር ውስጥ የታቀደው መጓጓዣ መንገድ ምን ዓይነት ነው?**

•አሁን በሚኒያፖሊስ ውስጥ የሚገኘውን የሃየዋታ መስመርን የመሰለ ቀላል የባቡር ሃዲድ ነው

**ሴንትራል ኮሪዶር የሚኔሶታ ነዋሪዎችን የሚጠቅማቸው በምን መንገድ ነው?**

• በሴንትራልና በሃየዋታ ኮሪዶሮች አካባቢ የሚሠሩ ተቀጣሪዎች (ኤርፖርቱን፣ ሞል ኦፍ አሜሪካን፣ ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ሚኔሶታንና ሴንት ፖል ሚድዌይን ጨምሮ) ሥራቸው ለመሄድ አስተማማኝ መንገድ ይኖራቸዋል

• LRT ወይም ቀላል የባቡር ሃዲድ መጓጓዣ እስከ 2030 ዓ.ም. ድረስ የተጓዥ ብዛት እስከ 43000 ይደርሳል ብሎ የወደፊቱን አመላክቷል

• ለትዊን ሲቲስ ነዋሪዎችና ጎብኝዎች ያነሰ የመኪና መጨናነቅ

• በሴንትራል ኮሪዶር ውስጥ የሚገኙ የንግድ ቦታዎች ከመጓጓዣ መሻሻል ጋር አብሮ የሚመጡትን እድገቶችና የተሻለ እይታ ጥቅም ያገኛሉ።

• የሕዝብ መጓጓዣ አደገኛ የመኪና ጭሶችን ይቀንሳል እንዲሁም የአየሩን ጥራት ይጨምራል

**ሴንትራል ኮሪዶር ውስጥ ለውጦች የሚያስፈልጉት ለምንድን ነው?**

• እስከ 2020 ዓ.ም. ድረስ የመኪና እንቅስቃሴ በ48 በመቶ አድጎ ከፍተኛ መጨናነቅ ይፈጥራል ተብሎ ይጠበቃል

• ኢንተርስቴት 94 በመሬት የተከበበ ስለሆነና እስከ 2020 ዓ.ም. የይዘት ገደቡን ያልፋል ተብሎ ስለሚጠበቅ ይዘቱን መጨመር ከ 1 ቢሊዮን ዶላር በላይ አስወጥቶ፣ በአካባቢው ያሉትን ሠፈሮች ጎድቶ መምጣቱ የማይቀረውን የመኪና መጨናነቅ ማዘግየት ብቻ ስለሆነ ውጤቱ።

• የሚድዌይ የንግድ ሠፈር በትዊን ሲቲስ ውስጥ በፍጥነት ከሚያድጉት የንግድና የመኖሪያ ሠፈሮች አንዱ ሲሆን የመኪና መጨናነቅ ከሚበዛባቸው ቦታዎችም አንዱ ነው።  የተሻለ መጓጓዣ መንገድ ሲኖር እድገቱ እንዲቀጥል ይረዳል።

• የዩኒቨርሲቲ አሸኑ አካባቢ ከትዊን ሲቲስ ቦታዎች ውስጥ ሁሉ የተሻለ የከተማ ልማት ሊኖረው የሚችል ቦታ ነው።

**ሴንትራል ኮሪዶር በክልሉ የመጓጓዣ መንገድ አሠራር ላይ የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው?**

• መጓጓዣ መንገድ በደንብ የሚሠራው ቁልፍ የሆኑ ቦታዎችን ሲያገናኝና አስቀድሞ ማወቅ የሚቻል ዓይነት አገልግሎት ሲሰጥ ነው።  ከሃየዋታ መስመር በተጨማሪ ተሻሽሎ የሚቀርበው ሴንትራል ኮሪዶር በትዊን ሲቲስ ውስጥ ያሉትን ትልልቅ የኤኮኖሚና መኖሪያ መድረሻዎችን አገናኝቶ በሠፈሮች አካባቢ አስቀድሞ ማወቅ የሚቻል ዓይነት መጓጓዣ ያቀርባል።

**የሴንትራል ኮሪዶር ወጪ ምን ያክል ይሆናል?**

• ሴንትራል ኮሪዶር ውስጥ ቀላል የባቡር ሃዲድ ማስገቢያ ዋና ገንዘብ 930 ሚሊዮን ዶላር ነው ተብሎ ታቅዷል።

**በይበልጥ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የሚከተለውን ይገናኙ፦**


Steve Morris, Transit Projects Manager (የመጓጓዣ እቅዶች አስተዳዳሪ)
Ramsey County Regional Railroad Authority
Suite 6560, RCGC-West,  50 West Kellogg Blvd.
St. Paul, MN 55102     651-266-2784
Steve.Morris@co.ramsey.mn.us     www.centralcorridor.org